# የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

**Amhara National Regional State Education Bureau**

☎ 0582204747 (222 1508) ✉ 764 FAX 0582220813


ቁጥር፦ትብ2/537/ስት-0.1
ቀን 20/11/2014 ዓ.ም

ለሁሉም ዞን ትምህርት መምሪያዎች
ለ6ቱ ከተማ አስተዳደር ትም/መምሪያዎች
<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፦ <u>የ2015 ዓ.ም የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ (ካሌንደር) ስለመላክ</u>

በሀገር አቀፍ ደረጃ በትምህርቱ ዘርፍ የተቀመጡ የትምህርት ግቦችን ለማሳካት በየአመቱ የትምህርት ዘመኑ አመታዊ <u>የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ (ካሌንደር)</u> ከሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በጋራ እየተዘጋጀ ተግባራዊ ሲደረግ መቆየቱ ይታወቃል።

በመሆኑም የ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን **<u>የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ (ካሌንደር)</u>** ከዚህ ደብዳቤ ጋር <u>5 ገፅ</u> አባሪ አድርገን በላክነው መሰረት እንዲፈፀም እያሳወቅን ወደፊት የሚደረጉ ማሻሻያዎች ካሉ የምናሳውቅ መሆኑን እናሳስባለን።

ከሠላምታ ጋር

መላኩ አበበ ፈንቴ
ምክትል ቢሮ ኃላፊ

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለም/ቢሮ ኃላፊ(.................................ዘርፍ)
- ለ-----------------------------------------ይሬክቶሬት

<u>ትም/ቢሮ</u>

# በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት
# ትምህርት ቢሮ

## የ2015 ዓ.ም የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ (ካሌንደር)

ትምህርት ቢሮ
ሀምሌ 2014 ዓ.ም
ባህር ዳር፤

# የ2015 ዓ.ም የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ (ካሌንደር)

## 1. መግቢያ

ትምህርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ በሀገራት ልዩ ትኩረት የተሰጠው ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡ በዓለማችን በምጣኔ ሀብት፣ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ያደጉ ሀገራት የእድገት መሰረታቸው ለትምህርት የተለየ ትኩረት በመስጠት ተገቢውን የሰው ኃይል፣ የማቴሪያልና የፋይናንስ ግብዓቶች በማሟላት ጠንክረው በመሥራታቸው ነው።

የትምህርት ውጤት የሚመጣው ጥራት ባለው እና ተገቢ የሚሆነው የክፍለ ጊዜ ብክነት ሳይኖር በተቀመጠው ትምህርት ጊዜ ሰሌዳ መሰጠት ሲችል ነው፡፡ የመማር ማስተማር ሂደቱ በመላ ሀገሪቱ ወጥነት ባለው የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ መመራት አለበት፡፡

በመሆኑም በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በሁሉም ዞን፣ ከተማ አስተዳደር እና ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ስር በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ነባራዊ ሁኔታውን ባገናዘበ መልኩ ተመሳሳይ ትምህርት አተገባበር እንዲኖር ይህ የትምህርት የጊዜ ሰሌዳ/ ካሌንደር ተዘጋጅቷል፡፡

በዚህም መሰረት ሁሉም ዞኖች፣ ከተማ አስተዳደሮች፣ ወረዳዎችና ትምህርት ቤቶች ግብአቶችን የማሟላት እና ሌሎች የቅድመ ዝግጅት ስራዎችን በማጠናቀቅ ወደ መማር ማስተማር ተግባር መግባት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 2. <u>በዓመቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት</u>

### 2.1. የ2015 ዓ.ም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት /ሴሚስተር/ የትምህርት ፕሮግራም

2.1.1. ነሀሴ 23/2014 ዓ.ም ጀምሮ መምህራን በት/ቤታቸው ተገኝተው የቅድመ ዝግጅት ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡

2.1.2. ከነሀሴ 23 እስከ ጳጉሜ 4/2014 ዓ.ም ድረስ የተማሪዎች ምዝገባ ይካዳል፡፡

2.1.3. መስከረም 2/2015 ዓ.ም ጀምሮ ትምህርት ቤት ክፍት ሆኖ ለስልጠና ኦሬንቴሽን የሚሰጥበት ቀን ይሆናል፡፡

2.1.4. ከመስከረም 3-6/2015 ዓ.ም ለአንደኛ ደረጃ (1-8ኛ ክፍል) መምህራን የአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የማስተዋወቅ ሥራ ይካሄዳል፡፡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የመደበኛ ትምህርት የሚያስተምሩ ይሆናል፡፡

2.1.5. መስከረም 9/2015 ዓ.ም በክፍል ውስጥ የመደበኛ ትምህርት (Day one-class one) የሚጀምርበት ሆኖ መደበኛ የሬዲዮና የቴሌቪዥንሥርጭትም ይጀምራል።

2.1.6. ከጥር15-19/2015 ዓ.ም የአንደኛ ወሰነ-ትምህርት (ሴሚስተር) ማጠቃለያ ፈተና የሚሰጥበት ጊዜ ይሆናል።

2.1.7. ከጥር 22-26/2015 ዓ.ም ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች ዝግ ሆነው የተማሪዎች ፈተና የሚታረምበትና ውጤት የሚጠናቀርበትና የሚገለፅበት ጊዜ ይሆናል፡፡

2.1.8. ከጥር 28-30/205 ዓ.ም ድረስ ት/ቤቶች የሴሚስቴሩን የተማሪዎች ውጤት ተንትነው ለወረዳ ይልካሉ፡፡ ዞን/ከተማ አስተዳደር ከወረዳዎች የተላከውን የተማሪዎችን ውጤት አጠቃሎና ተንትኖ ለክልል ይልካል፡፡

2.1.9. የ8ኛ ክፍል ክልል አቀፍ ፈተና ተፈታኝ ተማሪዎች ምዝገባ ወደፊት ክልሉ በሚያወጣው የምዝገባ ፕሮግራም መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

2.1.10. የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ተፈታኝ ተማሪዎች ምዝገባ ወደፊት ሀገር አቀፍ የፈተናና ምዘና አገልግሎት በሚያወጣው የምዝገባ ፕሮግራም መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## 2.2. የ2015 ዓ.ም የ2ኛው ወሰነ ትምህርት /ሴሚስተር/ፕሮግራም

2.2.1. ከጥር 29/2015 ጀምሮ የ2ኛዉ ወሰነ ትምህርት የሚጀምር ሆኖ የቴሌቪዥን ትምህርት ስርጭትም ይጀምራል፡፡

2.2.2. ከግንቦት 21-25/2015 ዓ.ም የ2ኛ ደረጃ መልቀቂያ (12ኛ ክፍል) ፈተና ይሰጣል፡፡

2.2.3. ከሰኔ 5-9/2015 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ክልል አቀፍ ፈተና ይሰጣል፡፡

2.2.4. ከሰኔ 12-16/2015 ዓ.ም የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ማጠቃለያ ፈተና ይሰጣል፡፡

- የ6ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና ይሰጣል፡፡

2.2.5. ከሰኔ 19-23/2015 ዓ.ም የፈተና ማረሚያ፤የውጤት ማጠቃለያና የሮስተር ማዘጋጃ ጊዜ ይሆናል፡፡

2.2.6. ከሰኔ 26-29/2015 ዓ.ም የሮስተር ማዘጋጃ እና የተማሪ ውጤት የሚገለፅበት ጊዜ ይሆናል፡፡

2.2.7. ሰኔ 30/2015 ዓ.ም ወላጆችና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ በተገኙበት የዓመቱ ትምህርት ማጠናቀቂያ በደማቅ ስነ-ስርዓት ይከናወናል፡፡

## የ2015 ዓ.ም የትምህርት የጊዜ ሠሌዳ

| የመስከረም ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 30 | | | | |

17 መስቀል

| የጥቅምት ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 28 | 29 | 30 | | |

| የህዳር ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| | | | 1 | 2 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

| የታህሳስ ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| | | | | |

| የጥር ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 29 | 30 | | | |

| የየካቲት ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| | | 1 | 2 | 3 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | |

23 የአድዋ ድል

| የመጋቢት ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| | | | | 1 |
| 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |

| የሚያዚያ ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 30 | | | | |

6 ስቅለት 23 የላብአደሮች ቀን 27 የአርበኞች ቀን

| የግንቦት ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 28 | 29 | 30 | | |

| የሰኔ ወር የትም/ቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | ዓርብ |
| | | | 1 | 2 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

22 ኢድአልደሐ/አረፋ

## 3. የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ቀናት

| የወሩ ቀናት ብዛት | | ምርመራ |
|---|---|---|
| መስከረም | 15 | የሁለተኛ ደረጃ መደበኛ ትምህርት 20 ቀናት ይሆናል፡፡ |
| ጥቅምት | 22 | |
| ህዳር | 22 | |
| ታህሣሥ | 20 | |
| ጥር | 9 | |
| **ድምር** | **88** | |

## 4. የሁለተኛው ወሰነ የትምህርት ቀናት

| የወሩ ቀናት ብዛት | | ምርመራ |
|---|---|---|
| ጥር | 2 | |
| የካቲት | 21 | |
| መጋቢት | 21 | |
| ሚያዝያ | 18 | |
| ግንቦት | 17 | የአንደኛ ደረጃ መደበኛ ትምህርት ቀናት 23 ይሆናል፡፡ |
| ሰኔ | 7 | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቀናት 7 ይሆናል፡፡ |
| **ድምር** | 86 | |

## 5. በ2015 ዓ.ም ትምህርት የሚሰጥባቸው ቀናት ብዛት

- የመጀመሪያዉ ወሰነ ትምህርት ቀናት 88 ናቸው፡፡
- የሁለተኛው ወሰነ ትምህርት ቀናት 86 ናቸው፡፡
- የአንደኛ ደረጃ መምህራን ስልጠና ቀናት 5 ናቸው፡፡
- የትምህርት ፈተናና ምዘና ስራ የሚከናወንባቸው ቀናት 20 ናቸው፡፡
- የተማሪ ውጤት ማጠናቀሪያ ቀናት 14 ናቸው፡፡
- የ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን አጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ክፍት የሚሆኑባቸው ቀናት 213 ናቸው፡፡

<u>ማሳሰቢያ</u>

- ከጥር 15-19/2015 ዓ.ም የአንደኛው መንፈቅ አመት ማጠቃለያ ፈተና የሚሰጥበትን ነው፡፡
- ከጥር 22-26/2015 ዓ.ም የፈተና ማጠናቀሪያ ጊዜ ይሆናሉ።
- ከግንቦት 21-25/2015 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና የሚሰጥበት ጊዜ ይሆናሉ።
- ከሰኔ 5 - 9/2015 ዓ.ም የ8ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና የሚካሄድ ጊዜ ይሆናል፡፡
- ከሰኔ 12-16/2015 ዓ.ም የሁለተኛ መንፈቅ አመት ማጠቃለያ ፈተና የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

## 6. በ2015 ዓ.ም ትምህርት የማይሰጥባቸው ቀናት

| ተ.ቁ | መደበኛ ትምህርት የማይሰጥባቸው ቀናት | ትምህርት የማይሰጥበት ምክንያት |
|---|---|---|
| 1 | መስከረም 17/2015 ዓ.ም | የመስቀል በዓል |
| 2 | ጥር 11/2015 ዓ.ም | የጥምቀት በዓል |
| 3 | የካቲት 23/2015 ዓ.ም | የዓድዋ በዓል |
| 4 | ሚያዚያ 6/2015 ዓ.ም | የስቅለት በዓል |
| 5 | ሚያዚያ 23/2015 ዓ.ም | የላብ አደሮች ቀን በዓል |
| 6 | ሚያዚያ 27/205 ዓ.ም | የኢትዮጵያ አርበኞች መታሰቢያ የድል በዓል |
| 7 | ሰኔ 22/2015 ዓ.ም | የኢድ-አልአደሃ-አረፋ በዓል |
| | **ድምር 7 ቀናት** | |

**ማሳሰቢያ፡-**

- የአጠቃላይ ትምህርት ቤቶች ትምህርት የሚጀመረው መስከረም 2 ይሆናል፡፡
- በትምህርትና ስልጠና ዩኒቨርስቲ የሚቆዩ መምህራን የባከነ ክፍለ ጊዜ ካለ የሚያካክሱ ይሆናል፡፡
- በጥቁር ቀለም የተቀቡ ቀናት በህዝባዊ የድልና ክብረ በዓላት ምክንያት ትምህርት የማይካሄድባቸው ቀናት ናቸው፡፡
- የክልላዊና የከፍተኛ ትምህርት መግቢያ ፈተና የሚሰጥበት ቀን ከፈተና መስጫ ጣቢያ ውጭ የሆኑ ትምህርት ቤቶች የመማር ማስተማር ስራውን እንዲያካሂዱ ይደረጋል፡፡